# ★ ዴሞክራሲያ ★

×××××××××××××××××××××××××××

× የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን ×

×××××××××××××××××××××××××××

ቅጽ:18 — ልዩ ዕትም ኅዳር 1987 ዓ.ም.


## ኢሕአፓ ዘሬም አንደተናንት

የኢሕአፓ ልሣን ስለነበርና ስለሆነ ዲሞክራሲያን ከኢሕአፓ፣ ኢሕአፓን ከዲሞክራሲያ ለይቶ ለማየት አይቻለም:: ኢሕአፓ ዋና ዋና አቋሞቹን፣ ፖሊሲዎቹን፣ አለፍ አለፍ ትንተናዎቹንና ጥናቶቹንም ለሕዝብ በዲሞክራሲያ ነበር የሚያሰውቀው:: ኢሕአፓ በተቻለው መጠን የዲሞክራሲያ በየወቅቱ መውጣትና መሠራጨት አንዳይቋረጥ ለማድረግ በጣም ይጥር ነበር:: ይህም ሆኖ አለፍ አለፍ ድርጅቱን ትለልቅ ችግሮች ሲገጥሙት ቀውጢ ሁኔታ ውስጥ ሲገባ የዲሞክራሲያ መውጣት የተቋረጠባቸው ወቅቶች ነበሩ:: አንዳንዴ ለአጭር ጊዜ አንዳንዴም ረዘም ላለ ወቀት:: ኢሕአፓ ህልው ሆኖ አያለና ሌሎች ሥራዎቹን እየሠራም ማለት ነው:: የአመራር አባላት በአንዱ ማዕከል እየተሰባሰቡ በዲሞክራሲያ ቀዳሚያና ትኩረት ሊሰጠው በሚገባው የፖለቲካ ጉዳይ ላይ በወቀቱ ዲሞ ይዘት መውጣት ያለበት ዜና ትንተና ጥናት ... ላይ መነጋገርና መወሰን ለዲሞ ኤዲቶሪያል ቦርዱና የህትመት ክፍል መመሪያና ሃሳብ መስጠት አስቸጋሪ ሲሆንባቸው ነው መውጣቱ የሚቋረጠው:: ለዲሞክራሲያ መውጣት ብቻ ሳይሆን ለይዘቱም ላቀራረቡም ከብደት ከመስጠትም ነው ጥንቃቄው:: ታዲያ በእንደዚህ ያሉ ወቅቶች ከአባላትና ደጋፊዎች ዲሞክራሲያ መውጣት አንዲጀምር ያልተቋረጠ ጥያቄ ግፊትና ማበረታታት ይዥጎደጎዳል:: አጠገበም አለጠገበ " አባካቹሁ ትንሽ ታገሡ/" የተለመደው የአመራሩ መልስ ነው:: ይህ መልስ ታዲያ ጠያቂዎቹን አያረካም::

እነሆ ባለፉት 3 /ሦስት/ ዓመቶች ኢሕአፓ ከደርግ መንግሥት ነፃ አውጥቶና አስተዳደርም መስርቶ የቀየባቸውንና ይንቀሳቀስባቸውም የነበሩትን አካባቢዎች የሕወሐት /ማሌሊት አመራር ከሕግሓኤ/ሻዕቢያ /ና ከሱዳን መንግሥት ጋር በመተባበር ከወረረና በጦርነት ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰበት በኋላ አንደገና አመቺ ሁኔታ እስከሚፈጠር የዲሞክራሲያ መውጣት ተቋርጦ ቆይቶ ነበር:: ሕወሓት ለረጅም ጊዜ በዲሞክራሲያ ኤዲቶሪያል ቦርድ ውስጥ ይሠሩ የነበሩትን አንደ ፀጋዬ ገብረ/መድኅን ያሉትን የኢሕአፓ የአመራር አባላትና የበዐርና የቋንቋ ሰዎች አንዲሁም ሌሎችን በርካታ ነባር ጓዶችን ማሰሩ አንዳንዶቹንም መግደሉ ... በሀገር ውስጥ ነፃውን አካባቢ ማዕከል አድርጎ ይሠራቸው በነበሩት አንዳንዱ ሥራዎቹ ላይ ትልቅ ጊዜያዊ መናጋት ፈጥሮበት ቆይቷል:: የሕወሓት/ማሌሊትና ገብረ—አበሮቹ ፍላጐት ለ17 /አሥራ ሰባት/ ዓመታት ሜዳ ሳይለቅ ተጥቀን ሳይፈታ ደርግንና ጠባብ=ብሔረተኞችን በጦርም በፖለቲካም የተፋለመውን ቀራጥና ብቁ አባላትም በትግል ሂደት ውስጥ ያፈራውን ኢሕአፓን መደምሰስና ማጥፋት ነው:: ይህ ፍላጐታቸው ግን ቀዥት እንደሆነባቸው እስከ ከርሠ=መቃብር ያሳዳቸዋል አንጂ ኢሕአፓ ከቶም በፍጹም አይጠፋም:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላትነቱን አምባገነንነቱን አጥፊነቱን እያረጋገጠ ወደ ዕለት=ሞቱ የሚንደረደረውን ሕወሓት/ማሌሊት ከነግሳንግሱ አንኮታኩቶ ለመጣል የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚያካሂደው ትግል አሁንም ወደፊትም አስተማማኝና ፍቱን መሣሪያ ሆኖ ለማገልገል—ኢሕአፓ የማይታጠፍ ቃሉን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዘሬም መልስ ይሰጣል:: ራሱንም መልሶ እያደራጀ፣ እያጠናከረ የበለጠ ቀጣይ መስዋዕት እያደረገ

../

ተግሉን እንደሚቀጥል ለጠላቶቹም ጭምር ማረጋገጥ ይፈልጋል::

ቀጣይነት ባለው መንገድ የሕወሓት/ማሌሊት ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን
በኢትዮጵያ መንግሥትነት ስም የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃብት ንብረት ጉልበት ...
በመጠቀም ኢሕአፓንና ኢሕአሠን ለማጥፋት በከተሞችና በገጠሮች ውስጥ ያልተቋ
ረጡ ዘመቻዎች እያደረገ ቆይቷል ቀጥሏልም:: በርካታ አባላቶችንና የቀድሞ አ
ባላትን ደጋፊዎቹን ተባባሪዎችን በጦር—ሜዳ የተማረኩበትን በጥርጣሬ የሚይዛ
ቸውን ... እየገደለበት በእስር እያማቀቀበት የአንዳንዶቹንም ደብዛቸውን
እያጠፋበት ነው ያለው:: የሕወሓት/ማሌሊት መሪዎች ደርግ የጨፈጨፋቸውን
ኢሕአፓዎች አስከሬን ከመቃብር እያስወጡ አዲስ ሙሾ አስደርድረው ወላጆችን
እያስለቀሱ በሰማዕታቶቻችን አፅም የፖለቲካ—ቁማር እያደረጉ አንገበረከከላቸሁም
ያሏቸውን ቆራጥና ከስታራ የኢሕአፓ አባላት ዛሬም እያሳደዱ መግደልን፣ማሰርን፣
ማሰቃየትን ይሁን ብለው፣ ተቀዳሚ ሥራቸው አድርገው ቀጥለውበታል:: ለሰው ልጆ
ች ነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለፍትኅ—ርትዕ ለዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች መከበር
በቅንነት ቆመው የማያውቁ፣ ሁሉንም ክቡር መርሆዎች በጊዜያዊ መጠቀሚያነትና መሣ
ሪያነት የሚያዩ፣ ቀጥፈት ሃሰትና ክህደት መለያቸው የሆኑ፣ ንዑድና ክቡር የሆኑ
የሰብዕና መከሰቻ ፀጋዎች በሙሉ የራቋቸውና በኋላ ቀርና ጉታቸ ጉሰኛነት እስተሳ
ሰብ የናወዘ አንጉል ተሸካሚ የሆኑት የትግራይ ትግሬኝ ጠባብ—ብሔረተኞች ኢሕአፓን
አጥብቀው የሚጠሉት ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን ባለው የማያወላውል አቋምና የኅብ
ረ—ብሔራዊዋን ኢትዮጵያ ሕዝቦች በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ጠንካራ አንድነት ምን
አልባት ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ፖለቲካ ድርጅቶች በበለጠ ሊያራምድና ሊያስቀጥል ይችላል
ብለው በማመናቸው ይመስለናል:: ታዲያ እነዚህ የዚያ ኢትዮጵያዊ ትውልድ እንከርዳ
ዶች ጥሬውን ምርት እንዲያጠፋ አንፈቅድላቸውም::

ዛሬ ሁኔታው ይጠይቃልና በህይወት ያሉት የኢሕአፓ አባላት ተፈላልገውና
ተጠራርተው ይበልጥ ይሰባሰባሉ:: የዛሬዎቹ በድርጅቱ ውስጥ በአባልነት የቀጠሉት
በተለያዩ ምክንያቶች በድክመት—ስህተቶች፣ በልዩነቶች ወይም ከቁጥጥራቸው ዉጪ በሆኑ
ምክንያቶች ከድርጅቱ ተለይተው የቆዩትን ቀድሞ የኢሠፓ ባለሥልጣን ዛሬ የጠባቦች
መሣሪያ ያልሆኑትን ሁሉ "ኢሕአፓ የሁላችንም ፍላጐትና ዕምነት መከሰቻ፣ የጋራ የትግል
መሣሪያችንም ስለሆነ፣ የእናንተን መሰባሰብ የሁላችሁንም አስተዋጽኦ ይፈልጋልና—ያቀራ
ኘንን የሕዝብ አደራ አብረን እንድንወጣ — እንሰባሰብ" ይላቸዋል:: በመጠከላችን
ሊኖሩ የሚችሉ ጥቃቅን ልዩነቶችን፣ አለመግባባቶችን ዋጥ አድርገን፣ ቂምና በቀልን
አስወግደን፣ በፊትም ለሕዝባችን መብት ክብርና ጥቅም ነበርና የተነሳነው፣ ያንን የደ
መር ነውን ነገር ገን ገና ያልተገባደደ ተግባራችንን አብረን እንቀጥል እንላለን::
ያለንን ተመክሮ፣ ዕውቀትና ችሎታ ሁሉ አሰባስበን፣ ኢሕአፓን አጠናክረን፣ በተደራጀ
መልክ ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን ከሌሎች መሰል ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር በመተባበር
እንነሳ::

ዛሬ ለረጅም ጊዜ ተቋርጦ የነበረውን የዲሞክራሲያ መልሶ መውጣት መጀመር፣
እንዲሁም የኢሕአፓን የፖለቲካ ፕሮግራም ተሻሽሎ መውጣት አጋጣሚ በመጠቀም የኢሕአፓን
መልሶ መደራጀትና መጠናከር አስፈላጊነት ይኸኛው የዲሞ ዕትም እንዲያተኩርበት አድርገ
ናል:: ተሰባስበን እንድናሰባስብ ተደራጅተን እንድናደራጅ ዲሞክራሲያ ጥሪውን ያቀርባ
ል::

ያኔ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ /ኢሕአፓ/ ህላዌውን ማንነቱንና ምንነቱን ለሕዝቡ ይፋ ባደረገበት በ1967 ዓ.ም. መጠረሻ "ለመሆኑ ኢ—ሀ—ባ የማን ልጅ ነው?" እያሉ ይጠይቁ የነበሩት ወላጆችና ዜጎች ጥቂት አልነበሩም:: ከአብራካቸው የተፈጠረ ቢሆንም አዲስ ነገር ነበር:: ታዲያ ማንነቱ ላይ ቶሎ ግልጽ ባይሆኑም የኢሕአፓ አባላት በመሆን የሚፎርፉት በርግጥም ልጆቻቸው መሆናቸውን እየዋሉ እያደሩ በዓይናቸው ሲያዩና በጆሮአቸው ሲሰሙ — ኢሕአፓም ያለ ጥርጥር የራሳቸውን ልጆች ያሰባሰበና ያቀፈ "ማሕበር" መሆኑን ጠበልና ጠዲቁ—ፖለቲካ ቢሆንም ተረድተው አንዳንዶቹ በሙሉ ልብ ሌሎችም "መቼም ከመሰላችሁ ..." እያሉና እያቀማሙ ልጆቻቸውን፣ የልጆቻቸው "ማሕበር" የሆነውን ኢሕአፓን መደገፍ መርዳት ማፍቀር መንከባከብ ... ጀመሩ:: በወቅቱ በሀገራችን ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ባለመኖሩ በኢሕአፓ የተሰባሰበው የዚያ ትውልድ ክፍል ከወላጆቹ ጋር እንኳን በይፋ፣ በግልጽ፣ በመድረክ ተወያይቶ እምነቱን፣ ፍላጎቱን፣ ዓላማውን፣ ስለሀገሪቷና ሕዝቦቿ ሁኔታዎች ያለውን አመለካከት፣ የመፍትሄ ሃሳቦቹን ... ገልጾና አስረድቶ የወላጆቹን ሃሳብ ደግሞ ለማዳመጥ አልቻለም ነበር:: ስለዚህም ከታሪክ፣ ከባህል፣ ከዕድሜ ብልጽግና፣ ከሥራ ተመክሮ ... የወላጆቹ ትውልድ ያካበተውን ዕውቀት በሚገባ ሊጠቀምበት አልተቻለውም:: የነበረው አፋኝ ንጉሣዊ ሥርዓት የወቅቱን ወጣት ትውልድ አብዮታዊ ክፍል ጠንካራ ጥላቻ በመላበሱ ወጣቱም ቀደምቱን ትውልድ ከሥርዓቱ አራማጆች ነጥሎ ለማየት ባለመቻሉ በተገኘው ቀዳዳ እያንዳንዱ የራሱን አመለካከት ወደ ሌላው መግፋት እንጂ—መልክ ያለው የሃሳብ ልውውጥና ውይይት ፍሬያማ ተባደል በሁለቱ ትውልዶች መሀል አልነበረም ማለት ይቀላል:: ስለዚህ ነው ዘመናዊ ትምህርት ከነበራቸው በቀር አነስተኛ ከሆኑት ወላጆች በስተቀር ስለፖለቲካ ፓርቲ ምንነት ባለማወቃቸው ልጆቻቸው የተደራጁበትን የፖለቲካ ፓርቲ ማንነት እንኳን በደንብ ለማወቅ ጊዜ የሚጠይቅ የሆነው:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብሶት የወለደውን ኢሕአፓን የራሳቸውን ልጅ "የማን ልጅ ነው?" ብለው የሚጠይቁበት — ሊያውቁ የሚገባቸውንና የሚችሉትን ነገር ሳያውቁት እንዲቀዩ የሚያደርግ ኋላቀርና ኢዲሞክራሲያዊ ሁኔታ በመኖሩ ከቀዳሚው ትውልድ ወደ ወጣቱ መተላለፍ የነበረባቸው ፀጋዎች በወግ ያለመሰናከል በትክክል ሊተላለፉ አልቻሉም:: ተቻሉ ቢሆን ምንኛ በጠቀሙ ነበር::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ፖለቲካ ድርጅት የራሱ ቀጥተኛ ተመክሮና ግንዛቤ አይኑረው እንጂ ለፖለቲካ ለመንግሥት ለአስተዳደራዊና የዳኝነት ሥርዓት ... አዲስ አልነበረም:: በኢትዮጵያችን ውስጥ ቤያንስ ከኢዛና ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ማኅበረሰቡ / በሙሉም ባይሆን / የተወሰነ ቅርጽ የሥልጣን ተዋረድና የአስተዳደር ግንኙነት የነበረው መንግሥታዊ—ፖለቲካ/ፖሊቲ/ባለቤት ሆኖ የኖረ በመሆኑ መንግሥትን ሥርዓትን ሥልጣንን አስተዳደርን ዳኝነትን የውሳኔዎችና የትዕዛዞች ተዋረድንና ማኅበረሰባዊ ግንኙነት ... ስለዚህም ፖለቲካን ሀገር በቀል የሆነውን ከሞላ=ጎደል ያውቃል:: ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ የሆነው በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ በመሰማራቱ ሳይሆን ቅርጹ፣ስያሜው፣ አመጣጡ፣ አሠራሩ፣ ... ከኢትዮጵያ ሕዝብ በየወቅቱ ግንዛቤ አኳያ አዲስ በመሆኑ ነበር:: የፖለቲካ ፓርቲ ነኝ አለ ፓርቲ አዲስ ነገር ነው:: መሪነቱን የያዘው ማዕከላዊ ኮሚቴ የሚባል አካል ነው አለ:: ሕዝቡ የሚያውቀው አገሌ የሚለው አንድ "ራስ" ወይም "ደጃዝማች" የማህበሩ መሪ ሆኖ ብቅ አላለም:. ይባስ ብሎ በምስጢር እንዲያውም "እንደ ዲያቢሎስ" ጨለማን ተገን አድርጉ ይሠራ ጀመሮ:— በኅቡዕ/ የቀደሞውን ወግና ሥርዓት ብሂልና ባህል ቀደምቱ ትውልድ በሚጠብቀው መልክ አልነበረም ያስተናገደው:: ይህም ይበልጥ ልዩ መስሎ እንዲታይ አደረገው :: ንጉሡን መሣፍንቱን መኳንንቱን ፊውዳሉን ሥርዓት ... ለምን እንደሚቃወም የሚያስረዳው በጽሁፎች ያውም በስውር በሚበተኑ አማካይነት ነበር:: በሥርዓቱ ውስጥ እንደተለመደው ተቃውሞን የሚገልጥበት መንገድና ስልት በቅኔ በግጥም በአንጉርጉሮ በአገቦና በአሽሙር አለሳሰና ሽፋፍኖ ብቻ ሳይሆን እንደጨንገር በሚሽነቁጡ ኃይለ ቃሎችም ነበር:: አዲስ የትግል ዘይቤ

ቀድሞ ያልተለመደ ስልት ነበር የተጠቀመው:: ኢሕአፓ ዓላማዎቹን የሚገልጥባቸው በፕሮግራሙ ያሰፈራቸው በጽሑፎቹ አማካይነት ሃሳቦቹን የሚገልጥባቸው ቋንቋዎችም አዳዲስ ነበሩ:: የመደብ ቅራኔ፣ ብዝበዛ፣ ላብአደር፣ ዲሞክራሲ፣ አብዮት፣ ሶሺያሊዝም:... ለአብዛኛው ሕዝብ አዳዲሶች ነበሩ:: እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ነበር ኢሕአፓ ለወላጆቹም አዲስ ያደረጉት:: ታዲያ ምንአለበት ህፃንም እኮ ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ አዲስ ነው—ያውም "እ ሪ ሪ .../"እያለ የሚመጣ እንግዳ ነበር:: ለመሆኑ የትኛዋ እናት ነች አዲስ ሆናባት ልጅን የምትጠላ? / /አዲስ መሆን ማለትም መጥፎ መሆን አይደለም::

የኢትዮጵያ እናቶች የልጆቻቸው ጥምረት ሆና በፖለቲካ መድረክ ብቅ ያለውን የሕዝቡን ጥያቄዎች አንግቦ የተነሣውን በቀንነትና በግልጽነትም ማስተጋባት የጀመረውን ልክ እንደዚያው ብላቴና ነው አቀፈው የሰሙት "የወፍ—ቋንቋ ነው እንዴ የሚናገረው? እያሉም፣ እንደማንኛውም ህፃን "እፍ—መፍታት አይቀርም"ብለው ይሆናል፣ የሚያሣያቸውን ምልክቶች ሁሉ ይረዱለት የነበር ይመስላል:: ኢህአፓን ከወላጆች መነጠል የማይቻል ነበር:: በእውነትም ልክ እንደስሙ ኢሕአፓ ሕዝባዊ ነበርና:: ተማሪውንና ቀሪውንም ወጣት አብዛኛውን በምትሃት የሳበው ይመስል ነበር:: ከኢትዮጵያ መምህራን በርከት ያሉት የኢሕአፓ አባላትና በተለያየ ደረጃ ቢሆንም ደጋፊዎች ሆነው ነበር:: ዝግ ብሎ ይሁን እንጂ በሠራተኛው ውስጥም ደህና መሠረት ጥሎ ነበር:: በተለያዩ ዘርፎች የተሠማሩ ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ምሁራን አባላቱና ደጋፊዎቹ ነበሩ:: ከመኮንኖችና ወታደሮች መሐከል እንኳን ሳይቀር የተወሰነው ክፍል ኢሕአፓን የሚያፈቅርና የሚደግፍ ነበር:: የዕድገትና ሰማት በኅብረት ዘማቾች አብዛኛዎቹ የወጣቱ ትውልድ አካል በመሆናቸው የኢሕአፓንም አቋሞች የሚደግፉ ስለነበሩ በገጠሮች ውስጥ የጀመሯቸው እንቅስቃሴዎች አርሶአደሩን ወደ ትግል ወደ ኢሕአፓም የሳቡ ነበሩ:: ኢሕአፓ ከሕዝቡ ጋር ለመዋድ ያደረጋቸው ጥረቶች ፍሬያማ ነበሩ::

ኢሕአፓ በስያሜው እንደሚገለፀው ሁሉ ገና ከእለት ጽንሡቱ ጀምሮ በይዘቱ በባህሪያቱና በተግባሩ የኢትዮጵያን ኅብረ—ብሔራዊ ሀገራዊነትና ቀጣይነቱንም... የሚገለጽ ነበር:: የአባላቱ ብሔረሰባዊ ስብጥር—ከትትል ከትልልቆች ብሔረሰቦችና ከትንንሾችም በስፋት ያካተተ፣ ሆኖም ሁሉም በኢትዮጵያዊነታቸው የተሰለፉበት ድርጅት፣ መስፈርቱ የፖለቲካ አመለካከት፣ የዓላማና የአስተሣሰብ አንድነት እንጂ ከአንዱ ወይም ከሌላው ብሔረሰብና አካባቢ መወለድ ያልሆነበት፣ አዲስ ዓይነት ወንድማማችነት/እህትማማችነት ጓዳዊነት፣ አዲስና ልዩ የሆነ የርስ—በርስ መተሣሰብና መፈቃቀድ፣ መቻቻልና መተማመን አባላትን ያቀራኘበት፣ ... ድርጅት በመሆኑም ነው ልዩ ስህበት የተቀዳጀው:: ማንም የኢሕአፓ አባል በብሔረሰቡ፣ በሃይማኖቱ፣ በጾታው፣... የተነሣ የሚደርስበት በደል ንቀትና ውርደት ወይም የሚያገኘው ልዩ ክብርና የበላይነት እንደማይኖር ተረድቶና አምኖ ነው የተሠለፈበት:: አባላቱ በፖለቲካ ዓላማቸው፣ በፕሮግራሙ ውስጥ በተከተቱ የጋራ የፖለቲካ እምነቶቻቸው፣ በሕግና ደንቦቹ ውስጥ በሰፈሩት፣ የአደረጃጀትና የአሠራር መተከሎቻቸው መሠረት ነው የተሰባሰቡት በፍጹም አጥንትና ደም ተቋጥረው አልነበረም::

ኢሕአፓ ደግሞ ለመሠረታዊ—ለውጥ የቆመ ድርጅት ነበር:: ዓላማውም በወቅቱ የነበረውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ .... ሁኔታዎችን መለወጥ፣ በምትካቸው ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የተሻሉ ሁኔታዎችን መፍጠር ነበር:: አመጠሪያው ውስጥ ያለው አብዮታዊ የሚለው ቃልም ይህንኑ መሠረታዊ—ለውጥ ፈላጊነቱን ገላጭ ነበር:: ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት፣ ወይም አልፍ አልፍ ይባል እንደነበረው " አዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት" ለማካሄድ ነበረ የተነሣው:: በረጅም ጊዜ ዓላማ ደረጃም ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አካሂደ" ለሶሻያሊዝም ምሥረታ ጉዞዬን እቀጥላለሁ" ይል ነበር:: ኢሕአፓ ለዲሞክራሲ ያለ ጥርጥር ታግሏል:: ሆኖም ይከተለው ከነበረው ርእዮተ ዓለም በመነጨ ትርጉሙና ግቡም ሁሉንም

ኢትዮጵያዊ ሣይሆን ሰፊውን ምዝብርና ጭቁን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት ማቀዳጀት
ነበር:: ያኔ ኢሕአፓ በላብአደሩ ፓርቲ ግንባር ቀደም መሪነት፣ በላብአደሩ
መደብም አምባገነንነት ያምን ስለነበር በማርክሳዊ ርእዩተ ዓለም ውስጣዊ ስሀ
ተቶች ሆነው የተገኙትን አስተሳሰቦችንም ያንፀባርቅና ያራምድ ነበር:: እነዚ
ህን የአንድ ፓርቲ ግንባር ቀደም መሪነትና የአንድ መደብ አምባገነናዊ ገዥነት
መርሆዎችን የለወጠው በ1976 ዓ.ም. ሁለተኛ ጉባዔውን ባካሄደበት ወቅት ነው::
ያኔ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ የመድበለ—ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት የሚ
ታገል መሆኑን በመወሰን በፕሮግራሙ ውስጥ ጭምር አስፍሮ ይህንኑ አቋሙን ከዚያን
ጊዜ ጀምሮ በይፋ የገለጸው:: ምንም እንኳን ይህንን አቋም የያዘው ገና እነጎር
ባቾብ "ግላሰኖስትና" "ፔሬስትሮይካ"፣... ብለው ሳይወጡ፣ ራሱ የኢትዮጵያንና
የዓለምንና የዓለምን ሁኔታዎች በማገናዘብ ቢሆንም ሃሣቡን በሰፊው ለማሳወቅ ያኔ
የነበረበት ሁኔታ አላስቻለውም:: "ዲሞክራሲያና" ሌሎችም ጽሑፎቹ የነበራቸው
ሥርጭት አነስተኛ በመሆኑ ለብዙ ኢትዮጵያውያን አስተሳሰቡን በሰፋት ለመግለጥ
የቻለው "ፊና ተ—ዲሞክራሲ" የተሰኘውን የራዲዮ ጣቢያ ካቋቋመበት ከሚያዝያ 22
ቀን 1982 ዓ.ም. በኋላ ነው:: ዛሬ ኢሕአፓ የሚታገለው ሁሉም ኢትዮጵያዊ
ሙሉ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቱን እንዲቀዳጅ ለማድረግ፣ ለማስቻል ነው:: ማን
ኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ምንም ዓይነት መብቱ . . እንዲነካበት፣ እንዲገደብበት አያስ. .
ፈልግም በሚል ጽኑ እምነት ላይ ቆሞ ነው የዛሬው ኢሕአፓ አዲስ—ገዥዎችን እየተፋለመ
ያለው:: እነዚያ፣ የአዲስ ቃላት ቀማታ አማርኛውን "የወፍ—ቋንቋ "አስመስለ
ውባቸው ገራ—ሲጋቡም የእናት ሆድ ሆኖባቸው ". አፍ መፈታቱ" አይቀርም እያሉ
በተሰፋ የተናገሩት እናቶች፣ ለካስ ልጆቻቸው አድገው፣ ጉልምሰው ይበልጥ አውቀው፣
ተመክሮ ገብይተው፣ ስህተቶቻቸውንም እንደሚያርሙ መጪውን አማትረው አይተው ኖሯል/?
ከእነዚያ ከትናንት ለጋ፣ አፍላ፣ ወጣት ኢሕአፓዎች መሐከል ከወታደራዊ ደርግ አረመኔ
አዊ ጭፍጨፋ የዳኑት፣ ከጠባብ—ብሔረተኞች የጥፋት ጥይት ደፍ እየተከላከሉ በትግል
የቆዩት፣ በተለያዩ ሥፍራዎች ከእስዓጆች፣ ከእስሪያዎችና ከገዓዩች አምልጠውና አድፍጠው
የቆዩት፣... ልጆቻቸው እነሆ ዛሬ በርግጥም "አፍ—ፈተተው ፣ በርግጥም ተምረው፣
አሽተውና—ጎምርተው፣ በአስተሳሰብም በሰለው ስህተት መፈፀማቸውን ተገንዝበውና አርመው፣
ዛሬም ከህዝቡ ጋር ወገነው እየተፋለሙ ናቸው:: በቀሰለ ልብ ሃዘኑን፣ ለቀሶውን፣
ስቃያውን፣... ተቋቁመው፣ የእነዚህ ድምር የጫነባቸውን አእምሮአዊና አካላዊ ህመም
ታግለው፣ ሞትን አባብለውና ሸንገለው እስካሁን የቆዩትን ወላጆች ኢሕአፓ አይዞአችሁ፣
ለጥፋቶቻችንና ስህተቶቻችን ይቅር—በሉን፣ የእናንተው ነገና ያቆያችሁልንን ኢትዮጵያ
ከጥፋት ለማዳን አሁንም አብረናችሁ ፍልሚያ ላይ ነን ይላቸዋል::

ኢሕአፓ ከአለተ ልደቱ ጀምሮ ለሕዝባዊ ባህሪው፣ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክ
ራሲያዊና ሰብአዊ መብት፣ ለጋራ ጥቅማቸው፣ለጋራ ፍላጐታቸው፣... ለመፋለም የወሰደውን
ጽኑ አቋም፣ የገባውን ቃለ—ኪዳን፣ ያደረገውን ፍጥምጥም ከፍተኛ ስፍራ ነው የሚሰጠው::
መሥራች አባላቱና በኋላም የተሰባሰቡበት አባላት በቀዳሚያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅር ያላ
ቸው፣ የሕዝቡ ታማኝ አገልጋዮች ለመሆንም የመረጡና የወሰኑ፣ ሕዝቡን አገለውትና ተከ
ተውት ሳይሆን ከጐኑ ቆመው አብረውት የሚፋለሙና በወገንተኛነትም የሚሟገቱለት፣...
መሆናቸውን በተቻለው መጠን እያረጋገጠ ነበር ያሰባሰባቸው:: ዛሬም እንደዚያው ነው::
ከዚያም በላይ አባላቱ ሕዝቡን በትሕትና እንዲያገለግሉ እያስተማረ የቀጠለ ድርጅት ነው::
የኢሕአፓ አባላት በነፍስ—ወከፍ ወደ ፓለቲካ፣ ወደ ኢሕአፓም የመጡት ለግል ጥቅም፣
ለሥልጣን፣ለዝና፣ ... ብለው አልነበረም፣ አይደለም':: ዓላማቸው ሕዝባቸውን፣ ወገናቸ
ውን ... ማገልገል፣ መርዳት፣ ማሻሻልና ማሳደግ ነበር፣ ነውም:: ዛሬም ኢሕአፓ ይዟ
ቸው የተነሳው የእነዚህ ዓላማዎቹ መሠረታዊ ይዘታቸው፣ የሕዝብን ጥቅምና—ፍላጐት ማስቀ
ደማቸው ላይ ሳይሆን ዝርዝር ማብራሪያቸው አተረጓጐማቸው ነው የተለወጠው:: ትናትም
ዛሬም ኢሕአፓ የቆመው ለኢትዮጵያ ሕዝቦች መብት፣ የጋራ ጥቅምና እድገት ነው:: ይህ

የኢሕአፓ ድርጅታዊ ህላዌ የተጠነጠነበት መሠረታዊ እምነት ነው:: ዛሬም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበር ጥቅምና ፍላጐት መጠበቅና መሟላት ኢሕአፓ በሚያካሂደው ሀገራዊ ትግል ውስጥ የሕዝቡ በርካታው ክፍል የሆነው የሰፊው ሕዝብ መብት ጥቅምና ፍላጐት ትልቅ ስፍራ ይይዛል:: ስለዚያ ለማኅበራዊ ፍትህ ቆምሁ ማለት ትርጉም ያጣልና::

ኢሕአፓ ለሰው ልጅ ባጠቃላይ፣ ከግለሰብ እስከ ማኅበረሰብ ላሉት ክፍሎችና ለመላው የአንድ—ሀገር ሕዝብም፣ ከሁኔታዎች ጋር የተገናዘበና የተጣጣመ፣ ሁለንተናዊ የሆኑ ገጽታዎችን አበክሮ የዳሰሰና ያጤነ፣ ወቅቱ የጠየቀውና የፈቀደው ማንኛውም ለውጥ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ይላል:: ስለዚያ የእድገትንና የመሻሻልን በር ገጥግጦ መዝጋት ሊሆን ይችላል:: በእኛ እምነት ለውጥ መደረግ ያለበት በአስፈላጊነቱ ሲታመንበት ነው፣ በአጥጋቢ ምክንያቶችም ላይ ተመሥርቶ:: አንዳንዴ አነስተኛ ማሻሻያዎች በቂ ሊሆኑ ሲችሉ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ጐላ ጐላ ያሉና ትልልቅ ለውጦች አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ:: አስፈላጊና ተገቢ ለውጦችን በወቅቱ አለማድረግ፣ ባለፉ ሁኔታዎች ውስጥ ጠንዝቶ፣ ግትር ብሎ ድፍን አድርጐ መቁጠጥ እድገትን ከመግታት አልፍ ጥፋትንም መጋበዝ ይሆናል:: በተለይም ጉልህ ለውጥ ማድረግ ማለት ውጪአዊ ነገሮችን ብቻ መለወጥ ሳይሆን በተመጣጣኝ ደረጃ የራሱንም፣ የድርጅቱን አባላት መለወጥ ጭምር የሚገለጥ ነው:: ርእዩተ ዓለምን፣ የፓለቲካ አመለካከትን፣ መርሆዎችን በከፊልም—ቢሆን መለወጥ ያለ ጥርጥር ጉልህ ለውጥ ነው:: የፓለቲካ ፕሮግራምን ማሻሻል ወይም መለወጥም እንደለውጡ መጠንና ዓይነት ቀለል ያለ ወይም ጉልህና ከበድ ያለ ሊሆን ይችላል:: ኢሕአፓ የተመሠረተበትን ሃያ ሁለተኛ ዓመት አሣልፍ የታወጀበትን 19ኛ ዓመት በሚያከብርበት ወቅት ነው:: ይህን ለሦስተኛ ጊዜ የተሻሻለ ፕሮግራሙን እያወጣ ነው:: በፕሮግራሙ ውስጥ ያደረጋቸው ለውጦች በአባላቱ አስፈላጊና ወቅታዊ ናቸው ተብሎ የታመነባቸውና በመጠንና ዓይነታቸውም ጉልህ የሆኑ ናቸው:: ወደፊት በሚወጡ የዲሞክራሲያ እትሞች ዋና ዋና ለውጦችን እያብራራን እንገልጣለን:: አንዳንዶቹም ጠቅለል ባለመልክ በፕሮግራሙ መግቢያ ውስጥ ተጠቁመዋል::

ኢሕአፓ በተለያዩ ምክንያቶች ከድርጅቱ ተለይተው የቆዩትን፣ በሁኔታዎች አለመመቻቸትና በሕወጣት አመቃ የተነሣ ከድርጅቱ ጋር እስካሁን ግንኙነት ያልፈጠሩትን፣ ነገር ግን አሁንም መሠረታዊ ዓላማቸውን እንደጠበቀ ያሉትን፣ በኢሠፓ ባለሥልጣናት ያላገለገሉትንና የሕወጠት መሣሪያዎች ያልሆኑትን የቀድሞ አባላት ጭምር አዲሱ ፕሮግራም ሊያሰባስብ ይችላል ብሎ ይገምታል፣ ይጠብቃልም:: በኢሕአፓ አባልነታቸው ቀጥለው፣ ሌሎች አዳዲስ አባላትንም እየመለመሉ ኢሕአፓን እንደ ድርጅት እስከ ዛሬ ህልው የትግል መሣሪያቸው አድርገው የቆዩት አባላት አብረዋቸው ለጋራ ዓላማ ተሰልፈው የነበሩትን የቀድሞ አባላት የጋራ ታሪክ ባለቤትነት ያውቃሉ፣ ይቀበላሉ:: እያንዳንዱ የቀድሞ አባል በድርጅቱና በትግሉ ውስጥ እስከነበረበት ወቅት ለተገኙት ድሎችና እድገቶች፣ እንደየሃላፊነት ደረጃው ደግሞ ለተፈፀሙ ስህተቶችና ድክመቶችም ባለድርሻ ነው እንላለን:: በጋራ ለያዝናቸው መሠረታዊ ዓላማዎች ተሠልፈው ሲታገሉ የወደቁት የሁላችንም ሰማእታት ናቸውና ታሪካዊ የክብር ሥፍራ ሰጥተን ሁላችንም እንዘክራቸዋለን:: በዚሁ ትግል ሂደት ውስጥ በየወቅቱ ጠላቶቻችን እጅ አካላዊ—ጉዳት፣ ዓእምሮአዊና መንፈሳዊ ችግር የደረሰባቸውን ለከፈሉት መስዋእትነት ተገቢውን ክብር እንሰጣለን፣ አቅምና ሁኔታችን ሲፈቅድም እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባቸዋል እንላለን:: ላመኑበት ዓላማ ተሰልፈው ሲፋለሙ የደርግና የጠባብ—ብሔረተኞች ሰለባ የሆኑ ጀግኖችና—አርበኞቻችን ናቸውና:: ኢሕአፓ በዚህ አጋጣሚ በኢሕአፓ፣ በኢሕአወሊ፣ በኢሕአሠ፣ በኢለአማ፣ ውስጥና ዙሪያ

ተሰለፈው ሲታገሉ ልጆቻቸው ለተሰውባቸው ወላጆች፣ የትዳር ጓደኞቻቸውን ላጡት
ሴቶችና ወንዶች፣ እህትና ወንድማቸውን ላጡት ወገኖች፣ ... ሁሉ" እግዚአብ
ሔር ያጥናችሁ እያለ የሰውአኑ ዓላማ ከቡር ሆኖ እንደቀጠለና እንደማይሞትም
ታሪካቸውም ህያው ሆኖ እንደሚኖር አብሮም በትህትና ማሳወቅ ይፈልጋል:: በድ
ርጅቱ የበላይ አካል፣ በድርጅቱ ውስጥ በተለያዩ ኃላፊነት ደረጃ ላይ በነበሩት
አባላቱም በተፈፀሙ ከባድና ቀላል ስህተቶች የተነሣ በሌሎች አባላትና ደጋፊዎች፣
በወላጆቻቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በዘመድና አዝማድ፣ ባጠቃላይም በሕዝቡ ላይ ለደረ
ሱት ጉዳቶች ሁሉ ኢሕአፓ ልባዊ ይቅርታ ይጠይቃል:: በሕዝብና በሀገር ፍቅር
ተነሣስቶ፣ የሕዝቡን የኑሮና ሕይወት ለማሻሻል፣ እድገትና ብልጽግና ለማምጣት፣...
ሕዝቡን መብት ለማቀዳጀት—በቅንነት አምሮ ሲታገል የተፈፀሙ ስህተቶች ናቸው::
ስተተት ድክመቶችን በተመለከተ በ1971 ዓ.ም. በአመራሩ ግምገማ ማድረግ ተጀምሮ
አባላቱም እንዲያሟሉት አንድ እንቅስቃሴ በ1972 ዓ.ም. ውስጥ ተደርጎ ነበር::
ከፍተኛ ድርጅታዊ ችግርና የበርካታ አባላትም ተረጋግቶ መቀየት አለመቻል ስለተከሰተ
በወቅቱ ሊጠቃለል አልቻለም:: ከዚያም በኋላ በየአጋጣሚያቹ ለጣቂ ርምጃዎች ሲወሰዱ
ቆይቷል:: የቀደሞ አባላት ይበልጥ መሰባሰብ ለግምገማ አርምት ተግባርችም ጥሩ አስተዋ
ጽኦ ሊያደርግ ይችላል ብለን እናምናለን::

የማንኛውም ድርጅት — ኢሕአፓንም ጨምሮ — ጥንካሬና ደካማነት የሚወሰነው
በአባላቱ ማንነት ነው:: ሁሉም አባላት ያለ ጥርጥር አስተዋፀኦ ይኖራቸዋል፣ ሆኖም
በድርጅቱ ውስጥ በኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ከዚያም በላይ በድርጅቱ ከፍተኛ የአመራር
አካል ውስጥ ያሉት አባላት ደግሞ የሚኖራቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተዋፀኦ
እንደዚያው እንዳሉበት የኃላፊነት ደረጃ ይተለቃል:: ኢሕአፓን ለመመሥረት፣ በአጭር
ጊዜ ውስጥ ለማሳደግና ለማጠናከር፣ በኢትዮጵያ ሕዝብም እንዲወደድ፣ እንዲታቀፍ፣ እን
ዲከበር፣... ለማድረግ የተቻለው እነዚያ በወቅቱ የነበሩት አባላቱ ባደረጉቸው ብርቱ
ጥረቶችና አዎንታዊ ሥራዎች መሠረት ነው:: ለስህተትና ድክመቶቹ ለደረሱት ጉዳቶችም
እነዚያው አባላቱ ናቸው የሚጠየቁት — ከሌሎቹ በበለጠ ደግሞ በአመራር ደረጃ ላይ
የነበሩት:: አሁንም ኢሕአፓን እያፈራን አዲስን መልሰን ለመገንባት ስንጥር የድርጅቱን
የወደፊት ጥንካሬና ድክመት፣ ብቃትና ተወዳጅነት፣ የሕዝቡን ቀጣይ ድጋፍ ማግኘት፣ ውጤታማ
ትግል ማድረግ፣ ... ወዘተ የሚወሰነው የአባላቱ ማንነት ነው:: አባላቱ ደግሞ የሚገ
ኙትና የሚወጡት ከሕዝቡ ውስጥ ነውና ጉዳዩ በየወቅቱ ሕዝቡ የሚገኝበትን ሁኔታም ይመለከ
ታል::

የፖለቲካ ድርጅት በርግጥ ግልጽ የሆነ ዓላማና የፖለቲካ ፕሮግራም ሊኖረው
ይገባል:: አባላቱም በዓላማውና በፕሮግራሙም አስፈላጊነት፣ ተገቢነት፣ ጠቃሚነት፣
ጠንካራ ዕምነት ሊኖራቸው ይገባል:: አለዚያ ትግል የሚጠይቀውን ውጣ ውረድ መቻልና
መስዋዕትነትን መቀበል አስቸጋሪ ይሆናል:: ማንኛውም አባል ዓላማውን በሚገባ ተረድቶ፣
ለስኬቱ አስፈላጊ የሆነውን ዝርዝር ፕሮግራሙን ነጥብ በነጥብ አምኖት ሲሰለፍ ነው እን
ደብቃቱ፣ ባለው ዕውቀትና ችሎታ፣ ሌላም ተሰጥኦና አቅም ድርጅቱን ለማጠናከር፣ በድርጅቱ
አማካይነትም ሕዝቡን ለማስተባበርና ለማታገል፣ ጠላትንም ለማዳከምና ለማቸነፍ ከፍተኛ አ
ስተዋጽኦ ለማድረግ የሚችለው:: ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል የትምህርትና የአስተዳደግ ዕድል
ስላልነበረውና ስለሌለውም ሁሉም የድርጅት አባላት በትምህርት፣ በሌላም ዕውቀት፣ በሥራ
ስምሪትና ተመክሮ፣ ... ወዘተ እኩል ላይሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን ህይወት ራስዋ
ትምህርት ቤት ስለሆነች—ሁሉም ያለማቋረጥ ይበልጥ ለማወቅ፣ ለመማር፣ ከጠሩ ራሳቸውን
በዕውቀት ማሳደግ ማሻሻልና ሁለንተናዊ ግንዛቤና ብቃት ማግኘት ይችላሉ:: ኢሕአፓ የሚ
ጠበቅበትን የትግል አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚችለው አባላቱ ብቁና ጠንካራ ሲሆኑ ነው::

../

በተጨማሪ የኢሕአፓ አባላት የቆሙለትን ዓላማ ለማሳካት የሚያደርጉት ትግልና የሚከፍሉት መስዋዕትነት ውጤታማ እንዲሆን ቀደም እንዳሉት የኢሕአፓ አባላት አርአያነታቸውን ተከትለው፣ የዛሬያቹና የወደፊቱ አባላት ቁርጠኝነትና ጽንዓት ዛሬም ወደፊትም ሊኖራቸው ይገባል:: "ዓለምን ድል ለማድረግ ከፈለግህ፣ በመጀመሪያ ራስህን አቸንፍ/" እንደሚለው አነጋገር፣ ከፊታችን የተደቀነውን መሰናክል ሁሉ ተወጥተን፣ ዓላማችንን ከግቡ ለማድረስ በቅድሚያ የእያንዳንዳችንን ድክመቶች መቆጣጠር፣ ማስወገድ ይኖርብናል::

ማንኛውም የኢሕአፓ አባል ጥሩና ትጉህ ተማሪ እንዲሁም ቶጉና ጠንካራ ሠራተኛ መሆን አለበት:: ትግሉ ውስብስብ ስለሆነ፣ ለሚገጥሙት ችግሮች፣ ለሚሰማራባቸው ተግባሮች ሁሉ ቀላል መፍትሔዎች፣ ዝርዝር መመሪያዎች አይኖሩትም:: የሁኔታዎች ተለዋዋጭነት የሚጠይቃቸው ተጨማሪ ተግባሮች ብዙውን ጊዜ ይኖራሉ:: ስለዚህ በተናጠልም ሆነ በቡድን አባላት የሚጠበቅባቸውን ለመወጣት ከዕውቀታቸው፣ ብቃታቸው፣ ... በተጨማሪ በራሳቸው በመተማመን፣ ሁኔታዎች የሚጠይቁትን ቀዳሚነት ወስደው ለመሥራት የሚችሉ መሆን አለባቸው:: ጥንቃቄ አስፈላጊ ቢሆንም የአባላትን አፍላቂነትና በራስ አነሣሽነት የሚገድል መሆን የለበትም::

የኢሕአፓ አባላት አብዛኛዎቹን ተግባሮቻቸውን ለማከናወን የሚችሉ ከሕዝቡ ጋር ሆነው፣ ሕዝቡን ስለ ጉዳዩ አስፈላጊነት አሳምነው፣ የሕዝቡን ድጋፍና ትብብር አግኝተው፣ ... ነው:: ይህን የሕዝብ ተሣትፎ ለማግኘት የሕዝቡን፣ልብ፣ የሕዝቡን ዕምነት ማግኘት ግድ ነው:: ይህ በኢሕአፓ አባላትና በሕዝቡ መሀከል መኖር ያለበት በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ከፍተኛ ሥነ–ምግባር ማሣየትን ከኢሕአፓ አባላት ይጠይቃል:: የሕዝቡን ክብር፣ መብት፣ ጥቅም፣ ሃብትና ንብረት፣ ባህልና ሃይማኖት፣... መጠበቅ፣ ማክበር፣ መንከባከብ እጅግ አጣም አስፈላጊ ነው::

የኢሕአፓ አባላት የቆሙለትን ዓላማ ለማራመድ የሚያደርጉት ትግል ስኬታማ እንዲሆን በዲሞክራሲያዊ መንገድ አጽድቀው የሚሰሩባቸውን ህገ–ፓርቲ፣ ውስጠ=ደንብና መመሪያዎች አክብረው ተከትለው መንቀሳቀስ፣ ኃላፊነትና ግዴታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል:: አለዚያ የተቀነባበረ፣ ቀጣይነት ያለው፣ እየጠነከረና እያደገ የሚሄድ ትግል ማድረግ አይቻልም:: የኢሕአፓ ህገ=ፓርቲ፣ ውስጠ=ደንብ፣ ዋና=ዋና መተከሎችን ያካተቱ መመሪያዎች የአባላትን መብቶችና ግዴታዎች በበቂና በዝርዝር ስለሚያሳውቁ ተግባራዊ ከሆኑ ውስጣዊ ዲሞክራሲንና የአባላትና በዕምነት ላይ የተመሠረተ ተሣትፎ ያረጋግጣሉ ብለን እናምናለን:: አባላት በድርጅቱ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታዎችን እያዳበሩ እንዲሄዱ ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ አለባቸው:: አባላት በፓርቲው አማካይነትም የሚያካሂዱት ትግል የሚሳካው የፓርቲው ዲሞክራሲያዊ ህይወት ተጠብቆ አባላት በሃሣብም ጭምር ሙሉ ተሣትፎ እያደረጉ በቅንነትና በኃላፊነት መንፈስ የገቡዋቸውን ግዴታዎችን ለመወጣት ሲጥሩ ነው:: እስከ ዛሬ ኢሕአፓ ውስጥ ስለውስጣዊ ዲሞክራሲ የነበረውን አመለካከትና አሠራር በተመለከተ የቀድሞ አባላትና አዳዲሶቹም ሊያጤኗቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ:: ይኸውም ኢሕአፓ በተለይ እስከ 1976 ዓ.ም. "ሁለተኛ ጉባዔው" ድረስ ጉልህ ማሻሻያዎች ሳያደርግ ይከተል የነበረው የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተ ዓለምንና በእሱ ውስጥ የተካተተን የአደረጃጀትና የአሠራር መርሆች ስለነበረ ስለዲሞክራሲ የነበረው ግንዛቤም፣ በተግባር አፈጻጸሙም የዚሁ ይከተለው የነበረው ርእዮተዓለም ገደቦች ነበሩበት:: በርከት ያሉ አባላት፣ የአመራር አባላትም ጭምር ለዲሞክራሲ መስፋት ፍላጎት ቢኖራቸውም፣ በውስጣዊ መድረኮች ስለዲሞክራሲ መስፈን ተገቢነት ተደጋግሞ ቢነሣም፣ በተወሰነ ደረጃ አድማሱን ለማስፋት ጥረቶች ቢደረጉም ርእዮተዓለማዊ መመሪያቸው በአባላትም፣ በአመራሩም ላይ የፈጠራቸው ተጽዕኖዎች ነበሩ:: በዚህ ክለል ግን የማይናቁ ጥረቶች ተደርገዋል:: በውስጣዊ መጽሔት አባላት የፈለጉትን እንዲጽፉ መድረክ ተከፍተ

ቀይ ሽብርና ሌሎች ቀውጢ ሁኔታዎች እስከሚያደናቅፉ ድረስ ለተወሰነ ጊዜ ሠር
ቷል:: በየስብሰባዎች ሀዋሶች፣ ኮሚቴዎች፣ ሴሚናሮችና ኮንፈረንሶች አባላት
ያለ ምንም ሥጋት ሃሳባቸውን ነፃ ሆነው ይገልጹ ነበር:; በተገቢ መድረኮች
ሃሳብን በመግለጽ ላይ ማእቀብ በድርጅቱ ውስጥ አልነበረም:: ኢሕአፓ ከ1967
ዓ.ም. ጀምሮ " ዋና ፀሐፊ" የሚባል ሥያሜ፣ ወይም "ሊቀ-መንበር" የሚል አጠ
ራር አምባገነናዊ አዝማሚያ ላላቸው ግለሰቦች በር-በመክፈት እና ሁኔታ በማመቻቸት
የተክለ-ሰውነት አደጋን ሊያመጣ ይችላል የሚል ስጋት ነበረው::
በዚሁ መንፈስ ከሁለተኛው ጉባዔ/1976/ በኋላም የአመራሩ አባላት በጋራ እንዲሰሩ
ነው ያደረገው::

ኢሕአፓ ነፃ ባወጣው አካባቢ ጉንደር ክፍለ=ሀገር ውስጥ በተካሄደው
የድርጅቱ ሁለተኛ ጉባዔ የሚኖሩበትና የሚገኙበት ሁኔታ ለመሳተፍ ያስቻላቸው አባ
ላት በልዑካናቸው አማካይነት ተሳትፈዋል:: የውይይት አጀንዳዎች ቀድመው ለአባ
ላት ተሰራጭተው ነበር:: ጉባዔው በተስማማባቸው አካሄዶችና ድምፀ አሰጣጥ መሠረት
ነበር:: አዲስ አመራር የተመረጠው በምስጥራዊ ድምጽ አሰጣጥ መንገድ በድምጽ ብልጫ
ነው:: አጩዎቹም የቀረቡትና የተገመገሙት በጉባዔው ተሣታፊዎች ነው:: ለመድበለ=
ፓርቲ ዲሞክራሲ እንደሚታገል ወስኖ በፕሮግራሙ ያሰፈረውና ፕሮግራሙንም ለሁለተኛ
ጊዜ ያሻሻለው በዚሁ ሁለተኛ ጉባዔው ነው::

የኢሕአፓ አባላት የቀድሞዎቹም ሆኑ የዛሬዎቹ በነበሩበትና ባሉበት ሁኔታ
የተወሠኑ መሰናክሎች ይደንቀፏቸው እንጂ ለዲሞክራሲ መስፈን፣ መከበር፣ መለምለም፣
መስፋት ከፍተኛ ፍላጎት የነበራቸውና ያላቸው ናቸው:: ይህን ስንል ግን የአብዛኛውን
አባላትን አይታ ለመግለጽ እንጂ ከኢሕአፓ አባላት መሐከል ፀረ-ዲሞክራሲ አዝማሚያ የነ
በረው ግለሰብ አልነበረም ለማለት አይደለም:: ዲሞክራሲያዊ አሠራርን በተመለከተም
በአካላትም ሆነ በአባላት ምንም ስህተቶች አልተፈፀሙም አንልም:: ዋናው መግለጫችን
ግን ለዲሞክራሲ ያለን ጠንካራ ፍላጎትና እውን እንዲሆንም ያደረግነውና እያደረግነው
ያለው ትግል ነው:: አሌ ከሚል ጋር በማስረጃ ለመነጣጠር ዝግጁ ነን:: ከፈረስና
በቀሉ እሰጥ-አገባ በመለስ/

የኢሕአፓ አባላት በድርጅታቸው አማካይነት እየታገሉ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ
ዲሞክራሲያዊ መብቱን እንዲቀዳጅ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነውን መስዋዕት ሁሉ ዛሬም
በመክፈል ላይ ናቸው:: የኢትዮጵያን ሕዝቦች እየዳመጠ ያለው የትግራይ-ትግሬን
ጠባብ ብሔረተኞች አምባገነናዊ አገዛዝ እንደጦር የሚፈራውን ለማጥፋትም እየተረባረበ
ያለውን ኢሕአፓን ሕጋዊ መብቱን ቀምቶት በፓለቲካ መድረክ እንዳይሳተፍ ስላገደው
አሁንም በሕገ-ወጥነትና /የወያኔ ሕግ-ሕግ ነው ከተባለ?/በህቡእ እንዲታገል ተገዷል::
አማቂ ከሆነው የወያኔ-ሻዕቢያ መንግሥት ስር፣ ከሰላዮች፣ ቀጥረኞችና አድርባዮች ...
ዓይንና ጆሮ ተሰውሮ ፓለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራዎችን ለመሥራት ተገድዷል:: ያለ ጥርጥር
ይህ ሁኔታ ኢሕአፓ በሁሉም ሰፍራ ውስጠዊ-ዲሞክራሲን በሚፈለገው መጠን እንዳያስፋፋና,
እንዳያዳብር ማእቀብ ፈጥሮበታል:: በርከት ያሉ አባላትን ርስበርስ ለማስተዋወቅ፣ ሰፋ
ባሉ መድረኮች ለመሰብሰብ፣ ነፃ ምርጫ እንዲያካሄዱ ለማድረግ ... ትልቅ እንቅፋት
ሆኖበታል:: አባላትም በሚያደርጉቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት
እንዳስፈላጊነቱ አሠራራቸውን አመጣጥነውና አጣጥመው ነው እየሠሩ ያሉት:: አሁን ያለው
ሁኔታ በትግል ሊወጥ የሚችልና የሚለወጥም መሆኑን ኢሕአፓ ያምናል:: ስለዚህም እመቃ
ው በጠነከረ ቀጥር ይበልጥ አምርሮና ቆርጦ መታገል፣ ለበለጠ መስዋእትም መዘጋጀት አስ
ፈላጊና ተገቢ ነው ይላል:: ነፃነት ንዑድ ስለሆነ ከቶም ዋጋው በዛበት አይባልምና::

ዋና ዓላማው ኢትዮጵያን ማፈራረስ የሆነው የትግራይ-ትግሬን ጠባብ ብሔረተኞች
አምባ ገነናዊ አገዛዝ ኅብረ-ብሔራዊቷዋን ኢትዮጵያ ለማጥፋት ቀዳሚያ የዚችን ኅብረ-ብሔ
ራዊት ኢትዮጵያ ህላዊ ገላጭና አራማጅ የሆኑትን ኅብረ-ብሔራዊ የፓለቲካ ድርጅቶች በማጥ
ፋት ላይ ነው የተሠማራው:: የመጀመሪያው ዓላማው ዒላማው ያደረገውም ኢሕአፓን ነው::

ገና አዲስ አበባን ሳይቆጣጠር ነው የወደፊት ዋና ጠላቱ ይሆናል ብሎ የፈረጀውን
ኢሕአፓን ለማጥፋት በጐጃምና በጐንደር የዘመተበት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በገጠ
ሮችና በከተሞች ኢሕአፓን ለማጥፋት ዘመቻውን እየቀጠለ ነው። የጦር ምርኮኞች
በእስር እየማቀቁ ናቸው። ከስ—አለተመሠረተባቸውም፤ ለፍርድ አልቀረቡም። በሱ
ዳኑ የበሺር መንግሥት ተጠልፈው ለወያኔ እስር ቤት የተዳረጉት የኢሕአፓ ነባር አ
ባላት አሁንም፤ በስደተኛነት ተጠልለው የመኖር መብት እንኳን አጥተው ፍትህ ተነፍ
ገው ከሁለት ዓመት በላይ በእስር እየማቀቁ ናቸው። የኢሕአፓ አባላት፤ የቀድሞ
አባላትና ደጋፊዎች በከተሞችና በገጠር በአምባገነናዊው የነመለስ መንግሥት እየተጠ
ለፉ በመታሰር ደብዛቸው እየጠፋ ነው። በአዲስ አበባና በአሥመራ ሥልጣን የጠ
በጠው የትግራይ—ትግሬኝ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን ኢሕአፓን ለማጥፋት ወስኖ እየተረባ
ረበበት መሆኑን አባላት በግልጽ መረዳት አለባቸው። ሕወሐት ሻዕቢያ ኢትዮጵያን
ለማጥፋት ኢሕአፓ ከእነሱ ጋር እንደማያብር፤ በህጋዊ ፖለቲካ መድረክም ሊመጥኑትና
ሊያሸንፉት እንደማይችሉ ተገንዝበው በኃይል፤ በጦርነት፤ በአመፃ ነው ሊያጠፉት እየሞ
ከሩ ያሉት። ኢሕአፓ በሃያ ሁለት ዓመት የትግል ዕድሜው ባፈራቸው አባላት ብቃትና
ጽንዓት ላይ ተመሥርቶ ስለሆነ የሚጓዘው — እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ አክ=እንትፍ
ያላቸው የወያኔ ሻዕቢያ መሪዎች ሌላም ኃይል ኢሕአፓን ማጥፋት አይችልም። የማንመ
ከን ሆነን እንጂ የደርግና የጠባቦች ጥይት መቸ በርደለን ያውቃል። ከአዲስ በሽታ
ይሰውረን እንጂ ነባሮቹን ሁሉ ተከተበናቸዋል። ጠባብ ብሔረተኞቹ ለማድረግ የቻሉት
ሕጋዊነት በመንፈግ፤ በህቡዕ እንዲሰራ በማስገደድ፤ የቀድሞ አባላትን በሰፊው እንዳያ
ሰባስብ፤ አዳዲሶችን በብዛት እንዳይመለምል፤ ለማስተባበር ምቹ ሁኔታ እንዳያገኝ ተሎ
እንዳይጠናከርና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን ሆኖ ግብአተ=መሬታቸውን እንዳያፋጥን ነው።
ይህስ ቢሆን እስከ መቼ? /

ይህ የዚህ ዕትም በኢሕአፓ በራሱ፤ በአባላቱ እምነት አመለካከት ማንነትና
በሚጠበቁባቸው ተግባሮች ላይ ነው ያተኮረው። ኢሕአፓ ስለ አባላቱ ሲናገር የትናንቶቹን
በተለያዩ ምክንያቶች ግንኙነታቸው ተቋርጦባቸው የቆዩትን፤ አሁን በድርጅቱ ውስጥ እየታገ
ሉ ያሉትን፤ ወደፊት መሰባሰብና ኢሕአፓን መልሰው ማጠናከር የሚፈልጉትን—የሚጠበቁትንም
ያካትታል። ድርጅታቸውን እየፈለጉም በሁኔታዎች አስገዳጅነት እስካሁን ከቀጣዩቹ ጋር
ለመገናኘት፤ ተመልሰው አብረው ለመሰለፍ ያልቻሉ ብዙ የቀድሞ አባላት ስላሉ በዚህ አጋ
ጣሚ መመናታት፤ ማቅማማት፤ በእስቲ እንየውና በእስቲ ነገ ከተግባራዊ የመደራጀት ተግባ
ር መቆጠብ፤ ወይም ባለፉ መለስተኛ ልዩነቶች፤ ቅሬታዎችና ስህተት=ድክመቶች በማተኮር
የወቀተን አብይ ተግባር መዘንጋት ወይም ማዘግየት አዲስና ጉልህ ስህተት ይሆናል እን
ላለን። ታሪካችንን አብረን እየጻፍን፤ ያለፉት ጉድለቶቻችንን ላዲሶቹ እየገለጥን፤ የቀ
ድሞ ስህተቶቻችንን በሰከነ ሁኔታ አብረን እየገመገምንና እየተማርንባቸው፤ ኢሕአፓን አ
ያደስንና እያረምን፤ ቀጣዩንና መጪውን ፍልሚያ በተፈተኑና በተማሩ አባሎቻችን እንድናጠ
ናክር እንሰባሰብ፤ እንደራጅ፤ እናደራጅ እንላለን። ራሳችንን በዕውቀትና በተመክሮ
እያሳደግንና እየበለጸግን፤ የጋን=መብራት ሳንሆን ባለን ትምህርትና ዕውቀት ሕዝባችንን
እያስተማርን ከታሪካችንና ከሕዝባችን የዳበረ ተመክሮና ዕውቀትም እየቀሰምን፤ ትናንት
እንዳደረግነው ዛሬም አፍቅረንና አምነነው ከጐኑ እንሠለፍ፤ ለመብቱ፤ ለክብሩ፤ ለነፃ
ነቱ፤ ለጥቅሙ፤ ለአንድነቱ፤ ... አብረነው በቁራጥነት እንታገል። ወትሮስ ህይወታች
ን ዳርገንለት የለ /